# ኢትዮ-ቻምበር የዜና መጽሄት

በኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የመረጃና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ የዜና መጽሄት

ቁጥር 175 ከሚያዝያ 16—30 ቀን 2011 ዓ.ም.


## በውስጥ ገጾች


- ምክር ቤቱ የጀርመን ... ገጽ 2
- ምክር ቤቱ የህንድ ... ገጽ 2
- የንግድ ሳምንቱ በሁለቱ ... ገጽ 3


# የኢትዮ-ሱዳን የንግድና የኢንቨስትመንት ፎረም ተካሄደ




በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና በኢፌዲሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ትብብር የተዘጋጀው የኢትዮ-ሱዳን የንግድና የኢንቨስትመንት ፎረም በኢሊሊ ሆቴል ሚያዝያ 21 ቀን 2011 ዓ.ም. ተካሄደ፡፡

በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ቋሚ ፀሀፊ አምባሳደር ደዋኖ ከዲር በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለፁት ኢትዮጵያና ሱዳን በተለይም በኢኮኖሚና በፖለቲካ ዘርፎች ያላቸው ግንኙነት ጠንካራና አዎንታዊ ነው፡፡ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነታቸውም በከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ መሆኑን አስታውሰው ሁለቱም አገሮች የሁለትዮሽ፣ ቀጠናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችን ጨምሮ የሚካፈሏቸውና የሚተባበሩባቸው የጋራ እሴቶች ያላቸው መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ምንም እንኳ ጠንካራና መልካም ግንኙነቶች ቢኖሯቸውም በኢኮኖሚና በቢዝነሱ ትስስራቸው ረገድ የበለጠ ሊሰራ እንደሚገባ አምባሳደሩ አሳስበዋል፡፡

የሱዳን የቢዝነስ ማህበር ተወካይ ዶ/ር ኢብራሂም አብዱከዲር በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት ጥልቅና ረጅም ታሪክ ያለው መሆኑን በመጥቀስ የሱዳንን ወደብ አለመጠቀም፣ በድምበሮች ላይ የነፃ ቀጠና አለመመስረት፣ ጥምር የባንክ አጠቃቀም ሲስተም አለመኖር እና የመሳሰሉት መሰናክሎች የሁለቱን አገሮች የንግድ ግንኙነት ሽባ ያደረጉ እነደሆኑ ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልዓኩ እዘዘው (ኢንጂነር) በበኩላቸው እንደተናገሩት በቅርብ አስርት አመታቶች በተለይም ከኮሜሳ መመስረት ወዲህ የኢትዮጵያና የሱዳን የግል ኩባንያዎች በሁለትዮሽ ንግዳቸው የጎላ መሻሻል አሳይተዋል፡፡ የሁለትዮሽ ንግዳቸው እየጨመረ ቢመጣም የሚጠበቀውን ያክል እንዳልሆነም ተናግረዋል፡፡ ሁለቱ አገሮች የኢኮኖሚ እምቅ አቅማቸውን በቀጠና ደረጃ ለማጠናከር የሚያደርጉትን ጥረት ለማሳደግ ፎረሙ እንደሚያግዝም ፕሬዚደንቱ ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በፎረሙ ላይ “ በኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት እድሎች፣ በኢትዮጵያ የንግድ እድሎች እንዲሁም በሱዳን የንግድና የኢንቨስትመንት እድሎች” በሚሉ ርዕሶች ላይ የፓወር ፖይንት ገለፃዎች የተደረጉ ሲሆን በሁለቱ አገሮች መካከል ባሉት የንግድና የኢንቨስትመንት እድሎች እና ባጋጠሙ ተግዳሮቶች ዙሪያ የፓናል ውይይት ተካሂዷል፡፡

በተለያዩ ዘርፎች ላይ የተሰማሩ የሱዳን የግል ኩባንያዎች ከኢትዮጵያ አቻዎቻቸው ጋር የአቻ ለአቻ ውይይቶችንም አድርገዋል፡፡

ከ100 በላይ የሚሆኑ የሁለቱም አገሮች የግል ኩባንያዎችና ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎች በንግድና የኢንቨስትመንት ፎረሙ ላይ ተሳትፈዋል፡፡

## ምክር ቤቱ የጀርመን ልዑካንን ተቀብሎ አነጋገረ



የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ፀሐፊ አቶ ውቤ መንግስቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የምክር ቤቱ የማነጅመንት አባላት ጋር በመሆን አምስት አባላት ያሉት የጀርመን ልዑካን ቡድንን ሚያዚያ 22 ቀን 2011 ዓ.ም. በምክር ቤቱ የቦርድ አዳራሽ ተቀብለው በጀርመን አገር ስለሚሰጠው የማናጀር ስልጠና ፕሮገራም ላይ አነጋገሩ፡፡

በጀርመን የዉጪ ጉዳዮች ሚኒስቴር የአውሮፓ ፖሊሲዎች ምክትል ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ሄንዝ ሄትመዬር ወደ ምክር ቤቱ የመጡበት ዋና አላማ በቢዝነስ ድርጅቶች ላይ ለተሰማሩ ከፍተኛ ሀላፊዎችና ስራ አስኪያጆች ስለሚሰጥ “ማናጀር ስልጠና ፕሮገራም” ስለሚባል የስልጠና እድል ለመወያየት መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ስልጠናው በኢትዮጵያ የግል ኩባንያዎች ውሥጥ የሚሰሩ ከፍተኛ የሆኑ የስራ አመራሮች ከውጪ አገር ከሚገኙ አጋር ኩባንያዎች ጋር የቢዝነስ ድርድር እና የቢዝነስ ውል ስምምነት ለማድረግ እና ከጀርመኖች ጋርም ቢዝነስ እንዴት እንደሚሰራ እውቀትና ክህሎት እንዲኖራቸው የሚያስችል ለአራት ሳምንታት ያክል በጀርመን አገር የሚሠጥ የስልጠና አይነት እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በጀርመን የዉጪ ጉዳዮች ሚኒስቴር የማናጀር ስልጠና ፕሮገራም የፕሮግራም ዳይሬክተር ሚስተር ሬይሙት ዱሪንግ እንደተናገሩት በኢዮጵያ ያሉ የንግዱ ማህበረሰብ ስለ ስልጠናው ፕሮግራም ምንነት እንዲያውቁ በማስተዋወቅ፣ የአመራረጥ ሂደቱን በማካሄድ እና ተወዳዳሪዎችን በመለየት ረገድ የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት እገዛ እንደሚያደርግ እምነታቸውን ገልፀዋል፡፡

አቶ ውቤ መንግስቱ በበኩላቸው ስልጠናው የንግዱ ማህበረሰብ በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን እዉቀትና ክህሎት ከማስጨበጥ ረገድ ጠቃሚ እንደሚሆን ተስፋቸውን ተናግረዋል፡፡ ምክር ቤቱ የንግዱ ማህበረሰብ ተወካይ እንደሆነና የተሰጠውንም ተግባር ለማከናወን አቅምና ብቃት እንዳለው ጨምረው ገልፀዋል፡፡ በቀጣይ ስለስልጠናው ከኢፌዲሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከኢፌዲሪ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ጋር መነጋገር እንደሚያስፈልግና ፕሮግራሙ ውጤታማ እንዲሆን የመግባቢያ ስምምነት በመፈራረም ዝርዝር የጋራ እቅድ ተዘጋጅቶ ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ እንደሚገባ ምክትል ዋና ፀሀፊው አሳስበዋል፡፡

ስለስልጠናው ፕሮግራም ምንነትና ጠቀሜታ፣ ለንግዱ ማህበረሰብ በማስተዋወቅና ተወዳደሪዎችን በመለየትና በመመልመል ምክር ቤቱ ትብብር በሚያደርግበት ረገድ እንዲሁም ተዛማጅ በሆኑ በርካታ ጉዳዮች ዙሪያ ሁለቱ ወገኖች ሰፊ ውይይት አካሂደዋል፡፡

የማናጀር ስልጠና ፕሮገራም በጀርምን የጀመረው የዛሬ 20 ዓመት ገደማ ከሩሲያ ጋር እንደሆነና በአሁኑ ወቀት 19 አጋር አገሮች እና 13,000 ማናጀሮች በስልጠናው የተሳተፉ መሆኑ ታውቋል፡፡

## ምክር ቤቱ የህንድ ልዑካን ቡድንን አነጋገረ





የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከህንድ ዓለም አቀፍ የጨርቃ ጨርቅ ማሽነሪ ኤግዚቢሽን ማህበረሰብ (India ITME Society) እና ከህንድ የንግድና ኢንቨስትመንት ለአፍሪካ ድጋፍ ከሚባሉ ድርጅቶች ተወካዮች ጋር ሚያዝያ 25 ቀን 2011 ዓ.ም. በምክር ቤቱ የቦርድ አዳራሽ ውይይት አደረገ፡፡

ኢ.ኤ.አ በ2020 አዲስ አበባ ስለሚካሄደው ዓለም አቀፍ የጨርቃ ጨርቅ ማሽነሪ አፍሪካ 2020 ኤግዚቢሽን አስመልክቶ በምክር ቤቱና አቻ ድርጅቶች ለተከናወኑትን ተግባራት የጋራ ኮሚቴው አመስግኗል፡፡ በመቀጠልም የድርጊት መርሃ-ግብሩን የገመገሙ ሲሆን በኤግዚቢሽኑ ወቅት ጎን ለጎን ስለሚካሄዱ ኩነቶችና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ዉይይት አካሂደዋል፡፡

# የንግድ ሳምንቱ በሁለቱ አገሮች የግል ኩባንያዎች መካከል ያለውን የንግድ ትብብር የበለጠ ያጠናክረዋል ተባለ




በቻይና ዓለም አቀፍ የንገድ ምክር ቤት፣ በኢፌዲሪ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒሰቴር፣ በኢፌዲሪ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እውቅና ተሰጥቶት በፐራና ኤቨንትስ እና በኤም አይ ኢቨንትስ ግሩፕ የተዘጋጀው 3ኛዉ የቻይና የንግድ ሳምንት በሚለንየም አዳራሽ ከሚያዝያ 24-26 ቀን 2011 ዓ.ም. ለንግድ ኅብኘዎች ክፍት ሆኖ ቆዬ፡፡

የኢፌዲሪ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚንስትር ደኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አረጋ በመክፈቻ ንግግራቸው እንደገለፁት የንግድና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ልማትን ለማላቅ በሚደረገው ተሳትፎ የኢትዮጵያ መንግስት የቻይናንን የንግድ ማህበረሰብ እንደ ጠንካራ አጋር ይቆጥረዋል፡፡ ኩነቱ ንግድ ኢንቨስትመንትና እንዱስትሪን ለማስፋፋት ብሎም የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ጨምረው ገልፀዋል፡፡

በኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚደንት መልዓኩ እዘዘው(ኢንጅነር) በበኩላቸው እንደተናገሩት ምክር ቤቱ እንደዚህ አይነት የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የግሉ ዘርፍ አንቀሳቃሾች አለም አቀፍ የሆኑ የንግድ ግንኙነቶችን ልምድ ለመካፈልና ትስስር ለመፍጠር የሚረዳቸው መልካም እድል እንዲኖር እያደረገ ነው፡፡ የንግድ ሳምንቱ የሁለቱን አገሮች የትብብር ግንኙነቶች የበለጠ የሚያጠናክር በመሆኑ ይህም ቻይና ከኢትዮጵያ ጋር የኢኮኖሚ ግንኙነቷን ለማሳደግ ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላት ያሳያል፡፡ ፕሬዚደንቱ አክለው እንደተናገሩት ኩነቱ በሁለቱ አገሮች የግል ኩባንያዎች መካከል ያለውን የንግድ የትብብር የበለጠ እንዲጠናከር ይረዳል፤ አዳዲስ የቢዝነስ እድሎችንም ይከፍታል፡፡

ሶስተኛው የቻይና የንግድ ሳምንት በቀላል ኢንዱስትሪዎችና ጨርቃጨርቅ፣ በግንባታ እቃዎችና ማሽኖች፣ በምግብና በመጠጥ ማቀነባበሪያ ቴክኖሎጂ፣ በቤት ዉስጥ መገልገያ እቃዎችና ፈርኒቸሮች፣ በሃይልና በብርሀን አማራጭ ምርቶች፣ በውበትና ጤና፣ በባዮኬሚካል እና በሞተር ተሽከርካሪ ክፍሎች እና መለዋወጫዎች ላይ የተሰማሩ ከ100 በላይ የቻይና ኩባንያዎች ምርቶቻቸውንና አገልግሎታቸውን ያቀረቡበት መድክ ሲሆን የኢትዮጵያ የንግዱ ማህበረሰብ ከቻይና አምራቾች እና የቴክኖሎጂ አቅራቢዎች ጋር በቀጥታ የተገናኘበትም እንደሆነ ታውቋል፡፡

## የኢትዮጵያ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የግልግል ማዕከል

አድራሻ፡- +251-115-31-10-15

ዋና አዘጋጅ፡- ደበበ አበበ
አዘጋጆች፡- ዮሴፍ ተሾመ
ጥበቡ ታዬ
ካሜራ፡- ያሬድ አባቡ

አድራሻ፡-
ስልክ-፡- +251-115-54-09-93
ፋክስ፡-+251-011-5517699
ኢሜል፡- ethchamb@ethionet.et
ድረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com